# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ( ኢሕአፓ)

## Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)

ሰኔ 29 ቀን 2003 ዓ.ም

## በረሃብ የተጎዳ ሕዝባችንን ለመታደግ እንረባረብ!!

እጣ ፈንታህ ነው ተብሎ የተፈረደበት ይመስል ከ3.5 ሚሊዮን በላይ የሚሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ በባለሙያዎቹ ገለፃ መሠረት በአፍሪካ ቀንድ አካባቢ ላለፉት 60 አመታት ያልታየ በዝናብ እጥረት ምክንያት የተከሰተው አስከፊ ድርቀት ኢትዮጵያንም በመጎብኘቱ ለረሃብና ረሃብ ነክ በሆኑ በሽታዎች እየተጠቃ መሆኑን የተለያዩ የዜና ተቋማት እየዘገቡ ይገኛሉ። በኑሮ ውድነት የተነሳም በየጊዜው እያሻቀበ የሚሄደው የምግብ ዋጋ ንረትም ችገሩን ለማባባስ የበኩሉን አስተዋፅዖ እያበረከተ ይገኛል። የእህል ዋጋ ማሻቀብን ለማስቆም የመለስ አገዛዝ በሚከተለው የተዛባና የተዘበራረቀ ፖሊሲ ምክንያት አልተቻለም። በኢትዮጵያ ካለፈው ግንቦት ወር ጀምሮ የፍጆታ ዋጋ ማመላከቻ ካለፈው አመት ጋር ሲነፃፀር 41 በመቶ መጨመሩ የዚሁ ውጤት ነው። የኑሮ ውድነትን ለማስታገስ ተብሎ እየተወሰዱ ያሉ እርምጃዎች ችግሩን ይበልጥ አባባሱት እንጂ መፍትሄ አልሆኑም።

የዚህ ድርቅና ረሃብ በዋናነት ተጠቂ የሆኑት ደግሞ ቀድሞውኑ ላለፉት በርካታ አመታት በተከታታይ እያሻቀበ ባለውና አብዛኛው ሕዝብ ከሚሸከመው በላይ በሆነው የኑሮ ውድነት የተነሳ በከፋ ድህነት የተጎዱ፤ በተለይም ሕጻናት፥ ቀያቸውን ለቀው ለመሄድ የማይችሉ ሽማግሌዎች አሮጊቶችና በበሽታ የደከሙት ናቸው። በዚህም የተነሳ በርካታዎች ሕይወታቸውን እያጡ እንደሆነ እየተነገረ ነው። በተለይ የሰብዓዊ እርዳታ ሰጪ ድርጅቶች ሊደርሱ በማይችሉበት አካባቢ ሁኔታው በጣም አሳሳቢ ደረጃ እየደረሰ ነው። በቅርቡ በምስራቅ ኢትዮጵያ ክልል ውስጥ በረሃብ እየሞቱ ያሉትን ዜጎቻችንን ለመታደግ እየተንቀሳቀሱ በነበሩት የተ.መ.ድርጅት የምግብ ፕሮግራም ሠራተኞች ላይ በደረሰባቸው ለሞት የዳረገ የጥቃት እርምጃ የተነሳ የነፍስ አድን ተግባሩን ለማቋረጥ መገደዱ በምሳሌነት ሊጠቀስ የሚችል ነው።

በሀገራችን በተለያዩ ክልሎች ውስጥ የተከሰተው ረሃብ ከፍተኛ እልቂት ማስከተሉ ሊደበቅ በማይችልበት ደረጃ ሆኖ ሳለ የመለስ አገዛዝ በቅድሚያና በአፋጣኝ የዜጎቻችንን ሕይወት መታደግ ሲገባው ዋና ትኩረቱ የሥልጣን ዘመኑን ማራዘሚያ የሚሆነውንና የባዕዳን ሎሌነቱን ለማረጋገጥ የሚያስችለው፣ ከ200 ሚሊዮን አይሮ በላይ ከጀርመን መንግሥት ባገኘው እርዳታ 200 ታንክ ከዩክሬኒያ መግዛቱ የሕዝብ ጠላትነቱን መስካሪና ጨካኝነቱንና ግድየለሽ ጠባዩን የሚያሳይ እርምጃ ነው። ከፉኛ ድርቅ በሚከሰትበት ወቅት 5.8 ሚሊዮን አይሮ ለማግኘት ከአንድ የአውሮፓ ኢንሹራንስ (የመድህን) ኩባንያ ጋር ተደረገ የተባለው ስምምነት ለምሳሌ እስካሁን ከምን እንደደረሰ የሚታወቅ ነገር የለም። የመጠባበቂያ ምግብ ከምችት አስተዳደርስ አከማቸሁ የሚለው እህል ለሚራቡት እንዲደርስ የማይደረግበት ምክንያቱስ ምንድን ነው? - ለክፉ ቀን የተባለው እህል በወያኔ መሸጡ የማይታወቅ ይመስል!

ስለተፈጥሮ የአየር ሁኔታ እውቀት ያካበቱ ሙያተኞች እንደሚገልፁት ከሆነ ችግሩ በይበልጥ ሊባባስ እንደሚችል ነው። በሰብዓዊ እርዳታ የተሰማሩ ድርጅቶች ከወራት በፊት በአካባቢው ለሚገኙ መንግሥታት ስለ ሁኔታው አስታውቀው ተገቢ እርምጃ ከወዲሁ እንዲወስዱ ጥሪ ቢያቀርቡም ሰሚ ጆሮ እንዳላገኙ ሁኔታው ይመሰክራል። ጠይቀን ያገኘነው 25 በመቶ ብቻ ስለሆነ ዳግም ጥያቄ ማቅረቡ ዋጋ ቢስ ነበር ማለት በጣር ላይ በሚገኙ ዜጎች ላይ የሞት ፍርድ ከመስጠት ውጪ የሚታይ አይሆንም። በሀገራችን ለተከሰተው የረሃብ አደጋ በምክንያትነት የዝናብ እጥረትን ለማቅረብ ቢሞከርም ዋናው ምክንያት ለሕዝብ ተጠያቂ፡ ግልፅነት ያለው፡ ሕዝብን አሳታፊ፡ የሕዝቡን ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶቹን አክባሪ የሆነ መልካም አስተዳደር እንዳይመሠረት በእንቅፋትነት ላለፉት 20 አመታት የተፈጠመውና በምዕራቡ ኃያላን መንግሥታት እየተደገፈ ያለው

የመለስ አገዛዝ እንደሆነ ነው። ይህ አገዛዝ እንዳሻው ለማደልና ለመቸብቸብ የሚያስችለው ሥልጣን በሞኖፖል መያዙና መሬትን በራሱ ሙሉ ቁጥጥር ሥር ማድረጉ ዋናው የችግሩ ምንጭ ነው። በተደጋጋሚ እንደታየው ካሁን በፊት የረሃብ እርዳታውን ለራሱ ፖለቲካ መጠቀሚያ ማድረጉም የታወቀ ነው። በሀገራችን አሁንም በበርካታ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎቻችን ሕይወታቸውን ለማቆየት በባዕዳን የምግብ እርዳታ ጥገኛ ናቸው። የመለስ አገዛዝ ከሥልጣን በተቆናጠጠበት ወቅት የኢትዮጵያ ሕዝብ በቀን ሶስት ጊዜ እራሱን ለመመገብ እንዲችል እናደርጋለን በማለት መጠነ ሰፊ ፕሮፓጋንዳ ቢነዛም ይኸው ከ20 አመት በኋላ ችግሩ ሊቀረፍ ቀርቶ እየተባባሰ ይገኛል።

የመለስ አገዛዝ በየጊዜው የገጠር ልማት ፖሊሲ አውጥቼ አገሪቷን በምግብ ራሷን ችላ ከምታመርተው እህል ወደ ውጭ የሚላክበት ሁኔታ እንዲፈጠር ጥረት እያደረኩኝ ነኝ ቢልም ተጨባጭ ውጤቱ ግን አሁንም የባዕዳንን እርዳታና የሰውን እጅ ከመጠበቅ ያልዳኑ ዜጎቻችን በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ናቸው። በከተማም ቢሆን ፆም አዳሪውና በረሃብ እየተጎዳ ያለው ሕዝብ ቁጥሩ ከፍተኛ ነው። በገጠር በተበላሸው የወያኔ የመሬትና እርሻ አቅዋም የተነሳ የመሠረተ ልማት አለመስፋፋት፤ በውሃ እጥረት ሳቢያ እተሰቃየ ያለውም ቁጥሩ የትየለሌ ነው። በየቀበሌው ተቋቋሙ ተብሎ የሚነገርላቸው የአርሶ አደር የሙያ ተቋማትም ቢሆኑ የገበሬውን ክህሎት ለማሻሻል እምብዛም የፈየዱት ነገር እንደሌለ የገበሬውን የኑሮ ሁኔታ እንዲሁም ምርት ለማምረትና ኑሮዉን ለማሸነፍ የሚጠቀምበትን የአገልግሎት መሳሪያዎችን መመልከቱ ብቻ በቂ ነው። የሴፍቲ ኔት የሚባለው እርዳታ ገንዘብ የማንን ኪስ እያደለበ እንደሆነም የሚታወቅ ነው። የተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤ ለፕሮፓጋንዳ ፍጆታ ካልሆነ በስተቀር በተግባር ውጤት አምጪ የሆነ እንቅስቃሴ አይደረግም። በባሌ፣ በቦረና፣ በኢሊባቡር፣ በከፋና በዳውሮ ለምሳሌ እየደረሱ ያሉ ውድመቶች የቀዬው ሰው ቀርቶ የዱር እንስሶቹ ሳይቀሩ እያሰሙ ያሉት የድረሱልን ጬኸት መልዕክቱ ሰሚ አለማግኘታቸውን ነው። ይህ ሁሉ የሚያሳየው ሕዝባችን ከድርቅና ከረሃብ ለመታደግ የሚያስችሉ ቀደም ብሎ መሰራት የነበረባቸው ተግባራት አለመሰራታቸውን ሲሆን ይህ አገዛዝ በሥልጣን ላይ እስካለ ድረስም ቀጣይ መሆኑን አመላካች እንደሆነ ነው።

በመሆኑም ካለፉት ተመክሮዎች በመነሳት አሁን የተከሰተው የረሃብ አደጋን ለመታደግና በረሃብተኛው ሕዝባችን ስም እየተለመነም ሆነ እየተለገሰ የሚገኝ እርዳታ በተገቢው መንገድ ለተራቡትና ለተጠቁት እንዲደርስ መደረጉን ማረጋገጥ ወሳኝ ነው። ወያኔ ካሁን በፊት ረሃብን ለመታደግ ተብሎ ከተገኘው በብዙ ሚሊዮን የአሜሪካን ብር ውስጥ አብዛኛውን የዘረፈ መሆኑ የሚታወቅ ነውና ይህ እንዳይደገም ዘዴ ማፈላለጉ አግባብነት ስላለው በእርዳታ ለጋሾች ላይም ሆነ በተግባር እርዳታውን ለማድረስ ለመንቀሳቀስ ችሎታ ባላቸው እንደ ተ.መ. ድርጅትና ሌሎች መንግሥታዊ ያልሆኑ ሕዝባዊ ድርጅቶች ላይ ጫና ለማድረግ መረባረብ ያስፈለጋል። ይህ አንዱ ገፅታው ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ከዚህ አዙሪት ለመውጣት ሁነኛ መፍትሄ የሆነው የመለስ አገዛዝን ከሥልጣን ለማስወገድ ቆርጦ መታገል ነውና ለዚህ ሁሉም ሀገር ወዳድ የበኩሉን አስተዋፅዖ ለማበርከት መንቀሳቀስ የሚጠበቅበት ይሆናል። ባዕዳን እርጥባን ከመለገስና የራሳቸውን ብሔራዊ ጥቅም ለማስጠበቅ ከመንቀሳቀስ ወጭ ለኛ ነፃነት መጎናፀፍ ሊታገሉ አይጠበቅባቸውም። በረሀቡም አሳበው ዝርፊያ ከወያኔ ጋር ሆነው ማካሄዳቸው ደግሞ የታየ ነው። የኤኮኖሚ ዕድገትን አመጣሁ ባዩ ወያኔ ከዚህ ቀደም እንደሰማነው ረሀቡ ድንበር አካባቢ ነው፣ ብዙዎችንም አላጠቃም ብሎ ችግሩን አቃሎ ሊያቀርብም እየጣረ ነው። በተከሰተው ረሀብም ሊጠቀም ቋምጧል። ይህንን ሁሉ ማክሸፍና ሕዝባችንን መታደግ ግዴታችን ነው።



EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel. 202-291-4217 Fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com

Website: www.EPRP.com

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France